

Seattle City Light

# የባለ ብዙ ቤተሰብ የ EV ኃይል መሙያ መርሃ ግብር

## ንብረትዎን ከባለሙያ እገዛ እና ማበረታቻዎች ጋር ለ EV ዝግጁ ያድርጉ

በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን (EV ዎችን) በባለ ብዙ ቤተሰብ ንብረትዎ ለመግጠም ይፈልጋሉ? Seattle City Light በታማኝ አማካሪዎች የ EV ኃይል መሙያ መፍትሄዎችን እንዲያቅዱ ሊያግዞት የሚችል ሲሆን በተጨማሪም ለመግጠም ዝግጁ በሚሆኑ ጊዜ የ EV ኃይል መሙያ ፕሮጀክትዎን ወጪ ዝቅ ለማድረግ አዳዲስ ቅናሾችን ያቀርባል።*

በየቀኑ፣ ብዙ አሽከርካሪዎች EV ዎችን እያሰቡና አመቺ የኃይል መሙያ አማራጮችን እየፈለጉ ነው። ስለዚህ፣ የዛሬ የ EV አሽከርካሪዎች እና ወደፊት EV ለሚያሽከረክሩ ነዋሪዎች የባለ ብዙ ቤተሰብ ንብረትዎን ማሻሻሉ ትርጉም የሚሰጥ ነው። የመጀመሪያውን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ በሚሆኑ ጊዜ City Light እርስዎን ለመርዳት እዚሁ አለ። የታማኝ አማካሪዎች ቡድናችን ስለንብረት ፍላጎቶችዎ በመረጃ የተደገፉ ምርጫዎችን እንዲያደርጉ **ለመደገፍ ነጻ እና የማያዳሉ ምክሮችን** ይሰጣል። እርስዎ የሚያስተዳድሯቸው አፓርትመንቶችም ይሁኑ ኮንዶሚኒየሞች፣ ተመጣጣኝም ቤቶችም ይሁኑ በገበያ ዋጋ ያሉ ቤቶች፣ የ EV ኃይል መሙያዎችን ለመግጠም በመረጃ የተደገፈ መንገድን ይፈጥሩ ዘንድ ልንረዳዎ እንችላለን።

### የ EV ኃይል መሙያዎችን የመግጠም ጥቅሞች

- EV ዎችን የሚያሽከረክሩ ነዋሪዎችን ወይንም EV ዎችን ለመንዳት እያሰቡ ያሉ ሰዎችን መደገፍ።
- የ EV ኃይል መሙያ ተደራሽነትን በማህበረሰቡ ውስጥ ማጠናከር።
- አዳዲስ ነዋሪዎችን በዘመናዊ መጠቀሚያዎች መሳብ።
- በአስተማማኝ ሁኔታ የኤሌክትሪክ መሰረት ልማትዎን ማሻሻል።
- ንጹህ መጓጓዣን መደገፍ።
- የአየር ጥራትን እና ማሻሻል እና የግሪን ሃውስ ጋዝ ልቀትን መቀነስ።



## ሁሉን ዓቀፍ<br>የ EV ኃይል መሙያ ግምገማን<br>በአራት ቀላል ደረጃዎች ያግኙ

1. **ከ EV ኃይል መሙያ አማካሪ ባለሙያ ጋር ለመገናኘት እኛን ያግኙን።**
2. ከኢንዱስትሪ ባለሙያ ጋር **ንብረትዎን ይገምግሙ።**
3. ለ EV መፍትሄዎች **ግለሰባዊ ምክሮችን ይወያዩ።**
4. የ EV መሰረተ ልማት የመግጠሚያ ወጪዎችን ለመቀነስ **የ City Light ማበረታቻዎችን ለማግኘት እገዛ ያግኙ።**

*የባለ ብዙ ቤተሰብ ንብረቶች በ EV ኃይል መሙያ መርሃ ግብር ላይ ለመሳተፍ ቢያንስ አምስት ዩኒቶች ሊኖሩዋቸው ይገባል።

Seattle City Light

# የባለ ብዙ ቤተሰብ የ EV ኃይል መሙያ ማበርታቻዎች

| የባለ ብዙ ቤተሰብ የ EV ኃይል መሙያ ማበርታቻዎች — ምን ያካትታል? | የቆጣሪ ፊት ለ ፊት መሰረተ ልማት | | | የቆጣሪ ጀርባ መሰረተ ልማት | የደምበኛ መሳሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የመገልገያ ማሰረጫ መረብ**<br>በ City Light ቁጥጥር የሚደረግበት | **የመገልገያ በፓድ የተገጠመ ትራንስፎርመር**<br>በ City Light ቁጥጥር የሚደረግበት | **ቆጣሪ**<br>በ City Light ቁጥጥር የሚደረግበት | **ፓነል**<br>በ City Light ቁጥጥር የሚደረግበት | **የ EV ኃይል መሙያ**<br>ደምበኛው በባለቤትነት የሚይዙት |
| አሁን የሚገኝ | | | | | |
| የ EV ኃይል መሙያ-ብቻ ማበረታቻዎች | | | | ● | ● |
| በኋላ ላይ በ 2023 የሚገኝ | | | | | |
| የዝግጁ-ያድርጉ ማበረታቻዎች | ● | ● | ● | ● | |

በተጨማሪም፣ ስለ ንብረት ፍላጎቶችዎ በመረጃ የተደገፈ ምርጫ እንዲያደርጉ የምክር አገልግሎቶች ይድረሱ። ለዝርዝሩ እኛን ያግኙን።

**የ EV ኃይል መሙያ-ብቻ**

የ EV ኃይል መሙያ-ብቻ በባለ ብዙ ቤተሰብ ንብረቶች ላይ ለተገጠሙ ኃይል መሙያዎች ማበረታቻዎችን ያቀርባል። ገንዘቦቹ የንድፍ፣ ፈቃድ፣ ግዢ እና (ደረጃ 1) እና/ወይንም የ EV ኃይል መሙያዎች (ደረጃ 2) የኃይል ማውጫ ገጠማ ወጪዎችን ለማካካስ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እንደ ጉልበት እና ቁሳቁስ ያሉ ተያያዥ ወጪዎችም ይሸፈናሉ። የመጨረሻው የገንዘብ መጠን ሊለያይ ይችላል።

**ዝግጁ ያድርጉ** (በኋላ ላይ በ 2023 የሚገኝ)

ዝግጁ ያድርጉ በባለ ብዙ ቤተሰብ ንብረቶች ላይ የ EV ኃይል መሙያዎችን ለማስተናገድ አዳዲስ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ማበረታቻዎችን ያቀርባል። አዳዲስ መሰረተ ልማት የሚያካትተው ፓነሎችን፣ ቆጣሪዎችን፣ ትራንስፎርመሮችን እና የተሻሻለ ማሰራጫን ነው። ገንዘቦቹ

ጉልበት እና ቁሳቁስን ጨምሮ ተያያዥ የፕሮጀክት ወጪዎችን ለማካካስ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። የመጨረሻው የገንዘብ መጠን ሊለያይ ይችላል።



## ንብረትዎን እንዴት አድርገው ከ EV ኃይል መሙያ ጋር ወደፊት ማስኬድ እንደሚችሉ በበለጠ ይወቁ።

ለማበረታቻዎች ብቁ ስለመሆን እና ስለ ነጻ ግምገማ ብሎም ትንተና ዝርዝር እኛን ያግኙን።

ICF MFEV_Flyer041323